# በታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ አመራር ወቅት የፌደራል መንግስት

# በአማራ ክልል የፈፀማቸው አበይት ተግባራት እና የታላቁ መሪያችን አሻራዎች ፡፡

## ክፍል አንድ

በፍስሀ ገመዳ Fishageda@gmail.com

ከአዲስ አበባ

በመጀመሪያ ለሁሉም የዚህን ፅሁፍ አንባቢያን፤ የታላቁ መሪ አድናቂዎች እና ተከታዮች እንዲሁም ቤተሰቦች የታላቁን መሪ መለስ ዜናዊ ይህችን የማቃትን ትንሽ ነገር ብቻ አንስቼ መፃፌ ቅር ሊያሰኝ ይችላል ብየ ስላሰብኩኝ በመጀመሪያ ይቅርታ እየጠየቅኩኝ ሁሌ እንደምለው ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና መረጃው ያላቸውና የመፃፍ ችሎታ ያላቸው ሰዎች አዳብረው ለህዝብ ያደርሱታል ብየ ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ የፁሁፌ ዓላማም በተለያዩ ወቅቶች ታላቁ መሪ በአማራ ክልል ምንም እንዳላደረጉ የሚገልፁ የተለያዩ ፀሀፊዎች በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች የሚያሰራጩ በመበርከታቸው ህዝቡን ማደናገር ብቻ ሳይሆን የህወሐት አጋር እና የኢህአዴግ መስራች የሆነው ብአዴን ከህዝብ በመነጠል በክልሉ ዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነተን ለማጎልበት የሚደረገውን ጥረት በማምከን አክራሪ ብሄርተኝነት ለማስፈን ወይም የነበረውን ብዝሀነትን የማይቀብል ስርአት እንዲሰፍን በመስበክ ላይ ያሉ የትምክህት ሀይሎች  አስተሳሰብ የበላይነት እንዲያገኝ ለማድረግ የታላቁን መሪ ስራዎችና የህዝብ ፍቅር ጥላሸት በመቀባት ላይ በማተኮራቸው እና እነዚህ የውሸት ሰም የማጥፋት ዘመቻዎች ላለፉት 26 አመታት የተካሄዱ በመሆናቸው ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍል ማደናገር ከመቻሉም በላይ ለእኩልነትና ዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት እንታገላለን ብለው የተሰለፉ አንዳንድ ሀይሎች አባላት ጭምር ያደናገረ ብቻ ሳይሆን ከመስመራቸው ያስወጣ ወይም ቀና የጉዞ መስመራቸው ላይ መንገራገጭ የበዛበት አስቸጋሪ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ክልሉ በአሁኑ ሰአት የህግ የበላይነት የራቀበት ጉልበተኞች እንደፈለጉ የሚፈነጩበት ማንም ሰው የፈለገውን መብላትና መጠጣት የማይችልበት ስርአት አልበኝነት የበላነይት የያዙበት ሁኖ እናገኘዋልን፡፡

አዛውንቶቹ የብአዴን መሪዎችም " ጥቂቶች ቆራጦች  ያልተንበረከከንው ነገ እልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው " ታረካዊ እና ዘመን ተሻጋሪ መፎክራቸው ትልቁ ጠላታቸው ደርግ መደምሰስ ያስቻላቸው እና እልፍ መሆናቸውም እውን ቢሆንም እልፍ የሆነው ኃይል ግን ባሰቡት እና የታገሉለትን ህዝባዊ መንገድ ይዞ ባለመጓዙ የታገሉለትና እንደመኖኩሴ ቆርበው እዚህ ያደረሱት ትግል መንገራገጭ በመጀመሩ ማረፍ በሚገባቸው ጊዜ እና ታሪካቸው ማካፈል በሚገባቸው ወቅት ድርጅታቸውን ለማዳን ልክ በወጣትነት

እድሜአቸው ሲያደርጉት አንደነበረው ሩጫና ከፍተኛ ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ እንግዲህ የትምክህተኞቹ ዋነኛ ዘመቻ የፌደራል ስርአቱ ማፈራረስ እና የድሮውን መመለስ ሲሆን ይህንን ለማሳካት ደግሞ ከኢትዮጲያ አልፎ አለአፍሪካ እና ለአለም የሚተርፍ ታላላቅ ተግባራት ፈፅመው ያለፉት ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ እና ድርጅታቸው ኢህአዴግ ለአማራ ክልል ይሁን ለኢትዮጵያ ምንም እንዳልሰሩ በመስበክ የጥላቻና የውሸት መአት በመዝራት ለአመታት የዘሩት ዘር ፍሬ አፍርቶ እንሆ ኢትዮጵያ አገራችን ዋጋ ማስከፈል ጀምሯል፡፡ በመሆኑም በታላቁ መሪ በአማራ ክልል ምንም እንዳልተሰራ የሚሰብኩ እና የሚያራምዱ ሐይሎች የሚታወቁትና የተለመዱት የተምክህት ሀይለች ብቻ ሳይሆኑ በዴሞክራሲያዊ ድርጅቱ ብአዴን ውስጥም ያሉ  በተለይ አዳዲሶቹ አባላት የጠላቶች አጀንዳ ራማጅ መሆን በመጀመራቸውና በክልላቸው እና በሀገረም ደረጃ ጉዳትም ማድረስ ስለጀመሩ እኔም በግሌ በአማራ ክልል በታላቁ መሪ ጊዜ የተሰሩ ወይም የተጀመሩ ስራዎች ምንድን ናቸው ብየ ማሰብ ጀመርኩኝ እናም የማቀውን እና የሰማሁትን የታላቁ መሪ የመጀመሪያ አሻራዎች በዚሁ ክልል ያሉትን እና ሀገራዊ ፋይዳቸው እጅግ ትልቅ (ስትራተጂክ ) የሆኑ ስራዎችን የማውቀውን ትንሽ ነገር ለማያቁት ለማካፈል ነው፡፡

የጽሁፌ ማጠንጠኛም በአማራ ክልል በመለስ አመራር በፌደራል መንግስት የተጀመሩ እና የተከናወኑ አበይት ተግባራት ውስጥ በሚከተሉት አበይት ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡

1. በግድቦች ዙሪያ

1.1 ለመስኖ አግልግሎት የሚውሉ ግድቦች(ቆጋ፤ እና ሌሎች ግድቦች)

1.2 ለኤሌክትሪካ አግልግሎ የሚውሉ ግድቦች(ጫራ ጫራ ግድብ፤ ጣና በለስ ወዘተ)

2. በግብርና ኤክስቴሽን ዙሪያ የመለስ ሚና (ቀናት የፈጁ ከመርዓዊ እና ከፎገራ አርሶ አደሮች ከታላቁ መሪ መለስ ጋር የተደረጉ ውይቶችና እና ለህገራዊ ስትራተጂ ቀረፃ የነበራቸው ሚና)

3. ባህርዳርን የአፍሪካ የሰላም ፎረም ማእከል ለማድርግ የተደረግ ጥረትበአማራ ክልል በድርቅ የተጎዱ አከባባዎች በማገዝ ዙሪያ( ከበለሳ እና ከሰቆጣ አርሶ አደሮች በችግሩ ዙሪያ የተደረጉ ውይይቶች)

4. በመንገድ ዙርያ (ከሰቆጣ-ላሊበላ-ኮን- መሀል ሜዳ አድርጎ አዲስ አባባ የሚያገናኝ መንገድ እና ወሎን እና ጎጃምን የሚያገናኝ እንዲሁም ሱዳን እና ጎንደር የሚያገኛኘው የአዘዞ - መተማ- ጋላባት (ሱዳን የሚያገናኘው)

5. የክልሉ የልማት ተቋማት ለማጠናከር የታላቁ መሪ የአመራር ሚና፡፡

## 1. በግድቦች ዙሪያ የተሰሩ

በአገር ደረጃ ለመስኖ አገልግሎት እና ለኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ እንዲውሉ ከታቀዱት እና ከተተገበሩት ግንባር ቀደሞቹ በዚህ ክልል (በአማራ ክልል) ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉትንን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 1.1 ለኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ አገልግሎት እና ለመስኖ የተሰሩ ግድቦች

በታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግስት በሀገር ደረጃ ከሰራቸው ትልልቅ ስራዎች ውስጥ የመጀመሪያውና እና በታላቁ ወንዞችን አባይ የመጠቀም መብታችን አይቀሬ መሆኑን ያበሰረው ታላቅ ስራ አንዱ የጫራ ጫራ ግድብ ነው፡፡

- የጫራ ጫራ ግድብ፡- በጣና አፍንጫ ወይም አፍ ማለትም ታላላቆቹ የአባይ ገባር ወንዞች ርብ፤ መገጭ፤ ጉማራ፤ ግልገል አባይ፤ ወዘተ በጣና ሀይቅ ላይ ከተሰባሰቡ በኃላ ወደ ግብፅ ለመጓዝ ጉዞ

የሚጀምሩበት መነሻ ቦታ ከባህርዳር ከተማ በስተሰሜን ምስራቅ በሚገኘው የታላቁ ወንዝ መነሻ ቦታ (አንዳንድ ፀሀፊዎች የአባይ መነሻ ስከላ የሚገነው ጭስ አባይ ነው ይላሉ) ሲሆን ግድቡ የጣናን ሀይቅ ከፍታ በአንድ ሜትር በመጨመር የአጭር ጊዜ አላማው የጭስ አባይ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ በደርግ የተሰረውና 18ሜጋዋት የሚያመነጨውን ወደ 80 ሜጋዋት ማሳደግ ሲሆን የሩቅ ወይም ዋነኛ አላማው ግን የጣና ውሀ አንድ ሜትር እንዲጨምር በማድረግ በምእራብ አቅጣጫ ያለውን ተራራ በመቆፈር የውስጥ ለውስጥ ዋሻ በመስራት የጣና በለስ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመጫ በተራራው ሆድ ውስጥ በመስራት ውህው 420 ሜጋዋት አሌክትሪክ ሀይል ካመነጨ በኃላ በምእራብ በኩል የተንጣለለውን ሜዳ መሬት ከሁለት መቶ ሺ በላይ ሄክታር መሬት መስኖ እንዲያለማ የተሰራ ሲሆን በአሁኑ ሰአት የጣና በለስ ስኳር ፕሮጀክት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

✓ ይህ ግድብ ኢናርን በተባለ የዩጎዝላብያ የግንባታ/ኮንስትራክሽን ኩባንያ ከሀገር በቀሉ ሱር ኮነስትራክሽን ጋር በመተባበር የተሰራ ሲሆን በኔ እምነት የኢህአዴግ መንግስት የአባይ ወንዝ ከዋናው መስመሩ አቅጣጫ በማስቀየር ትልቅ ስራ የሰራበት እና ከፍተኛ ልምድና የይቻላል መንፈስ ያጎለበት ትልቅ ስራ ነው ብየ አምናለሁኝ፡፡ ይህ ልምድ እና አቅም የፈጠረ ሲሆን የህዳሴው ግድብ ለመስራት አንድ ትልቅ እተዋጽኦ የፈጠረ ስራ ነው ብየ አስባለሁኝ፡፡

### 1.2 ለመስኖ ስራ ብቻ የተሰሩ ግድቦች

- የቆጋ መስኖ ፕሮጀክት
- ሌሎች በአባይ ገባር ወንዞች የታቀዱ/ የተጀመሩ ግድቦች
- ርብ፤ መገጭ ወዘተ

የቆጋ የመስኖ ግድብ 6000 (ከስድስት ሺ) ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ ለማልማት ታስቦ ለጀመሪያ ጊዜ በአባይ ገባር ወንዝ ላይ ከ700 ሚሊዮን ብር በሆነ ወጪ የተነባ ሲሆን ይህም በአባይ የመጠቀም መብታችን ያረጋገጠ ትልቅ ስራ ሲሆን ግድቡ ተጠናቆ የአከባቢው (የወረዳው) አርሶ አደሮች እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ በእርግጥ ሙሉ በሙሉ ህዝቡ እንዳልተጠቀመበትና እንዳንዱም የመስኖ እርሻው የባህርዛፍ ተክል እየተከለ በመስኖ አጠቃቀም ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ሲሆኑ የክልሉ መንግስት በዚህ ዙሪያ እየሰራ ያለውን ስራ አጠናክሮ በመቀጠል የመሬት አጠቃቀሙን ማስተካከል ይገባል፡፡

## 2 በግብርና ኤክስቴሽን ዙሪያ የመለስ ሚና (ቀናት የፈጁ ከመርዓዊ እና ከፎገራ አርሶ አደሮች ከታላቁ መሪ መለስ ጋር የተደረጉ ውይቶችና እና ለሀገራዊ ስትራተጂ ቀረፃ የነበራቸው ሚና)

በ1987/88 ዓ.ም የምርት ዘመን ሀገራችን የጀመረችውን አዲስ ሀገራዊ የኤክስቴንሽን መርሀግብር ለመገምገምና በላቀ ደረጃ ለማስኬድ ህዳር 1988 ዓ.ም በአማራ ክልል በመራዊ ከተማ ለአንድ ቀን እንዲሁም በፎገራ ወረዳ ወረታ ከተማ ደግሞ ለሁለት ቀን ከአከባቢው አርሶ አደሮች እና ባለመያዎች ጋር የወቅቱ የአማራ ርእሰ መስተዳድር የነበሩት የተከበሩ አቶ አዲሱ ለገሰ እና የተከበሩ አቶ በረከት ስምኦን በተገኙበት የምክክር መድረክ ተካሂዶ ነበር፡፡ በነዚህ ሁለት ከተሞች በተካሄደው ሀገራዊ ጠቀሜታ የነበረው ታላቅ መድረክ ታላቁ መለስ ዜናዊ ተገኝተው ከአርሶ አደሮቹ እና የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል ከሚተጉ የግብርና ባለሙያዎች ለሶስት ተከታታይ ቀናት ምክክር አድርጓል፡፡ በዚሁ መድርከ ታላቁ መሪ ከአርሶ አደሩ እና ባለሙያዎች ከተጨባጭ ሁኔታዎች ተጨባጭ ትምህርት አግኝቷል፤ አርሶአደሮቹ እና ባለሙያዎችም ከታላቁ መሪ ብዙ ትምህርት እና የስራ መመሪያ ተቀብሏል፡፡ እንግዲህ በታሪካችን መሪዎቻችን አንዲህ ወረድ ብለው ከአርሶ አደሩ ጋር መክረው ዘክረው ፓሊሲ አፈፃፀም ሲገመግሙና ፓሊሲዎቻቸውን ሲያሻሽሉ አይታወቅም ነገር ግን ታላቁ መሪ ግን እንዲህ አርሶ አደሩ ጋር ሶስት ተከታታይ ቀናት በመመካከር ሀገራችን አሁን ለደረሰችበትና ባለፈው አመት ያጋጠመን እጅግ አስከፊ ድርቅ አስከፊ እልቂት ሳያስከትል ብቻ ሳይሆን የአንድም ሰው ሂወት በርሀብ ምክንያት ሳያልፍ እንድንሸጋገር ያስቻለንን ታላቅ መሰረት ጥለው አልፏል፡፡ በነገራችን ይህ ተግባር በተለያዩ የታላቁ መሪ በተሰሩ ዶክመንተሪ ፊልሞች አይታይም ልክ የህዳሴው ግድብ የመሰረት ድንጋይ አስቀምጠው ሲመለሱ አውሮፕላን ውስጥ ቃለመጠይቅ ላደረገላቸው አብዲ ከማል የመሰረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ ምን ተሰማዎት ብሎ ለጠየቃቸው ሲመልሱ "ያቺ ድንጋይ ለኔ የኃፍረትና የውርደት ካባ ጥየ እንደመጣሁኝ ተሰምቶኛል " ያሉትን አንድ ቃል አይታዩም፡፡

ይቀጥላል!!!